# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ ቅጽ 40 ቁ.7 ሚያዚያ 2007 ዓ.ም.

## የኢሕአፓ--43 የትግል ዓመታት ሲቃኙ

ኢሕአፓ የሚወዷት አገራቸው ከጭቆና፤ ከብዝበዛና ከግፍ አገዛዝ የተላቀቀች እንድትሆን ጽኑ ምኞትና እምነት በነበራቸው፤ በአዲስ ሥርዓትና መንፈስ ሕዝቡ የሚገባውን የኑሮ ደረጃና ክብር እንዲጎናጸፍ ለማድረግ ቆርጠው በተነሱ፤ ከመላው ኢትዮጵያ በተውጣጡ ውድና ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች የተመሠረተ የትግል ድርጅት ነው። ኢሕአፓን የመሠረቱት በዚያ የታሪክ ምዕራፍ ወቅት የነበረው አገዛዝ ግዙፉነቱና አንጻራዊ ጥንካሬው ሳይስፈራቸው፤ ለህይወታቸውና ለምቾታቸው ሳይሳሱ የአዲስ ሥርዓት ምስረታን ዓላማችን ነው ብለው አንገበው የተነሱ ቆራጥ ጀግኖች ነበሩ። የኢሕአፓን የምስረታ ሂደትና ሁኔታ ታሪክ አወላግደውና ሀሰትን ጨምረው የሚያቀርቡት ሁሉ መማር ያለባቸው ሐቅ ይህ ነው።

የኢሕአፓ አባላት የሚወዱዋት እናት አገራቸውን በዝናና በታሪክ ብቻ ሳይሆን በሥልጣኔም ሆነ በዕድገት በዓለም ቀደምት ከሆኑት ሀገሮች ተርታ የምትደርስበትን ፤ ሕዝባቸው ከድኽነትና ከኋላቀርነት የሚላቀቁበትን፣ ፍትኅና እኩልነት የሚሰፍንበትን ክቡር ዓላማና ብሩህ ተስፋን ይዘው፤ በአገር ሉዓላዊነትና በሕዝባዊ ፍቅር ስሜትና እምነት መርህ ላይ ተሣሥረውና የተጠናከረ ኅብረ ብሔራዊ ጥምረት ፈጥረው ታግለዋል። የራሳችውን ፍርሃት አስወግደው፤ የግል ምቾታቸውንና ጥቅማቸውን ለአገርና ለወገን አሳልፈው ሰጥተው መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት ተሰልፈዋል ። እነዚያ በኢሕአፓ ውስጥና በኢሕአፓ ዙሪያ በቅንነትና በቆራጥነት የተሰለፉት ታጋዮች በእርግጥም የመላው ሕዝብ ብርቅዬ ልጆች ነበሩ። የዚያ ትውልድ የተማረ ክፍል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንዴት

መለወጥ እንደሚቻል አምርሮና አጠንክሮ መጠየቅ ሲጀምር ፤ የሀገሩን የቅርብና የሩቅ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለመረዳት እድሜውና እውቀቱ የፈቀደለትን ከማየትና ከማገናዘብ አልፎ አንግቧቸው የተነሳው የዲሞክራሲ ጥያቄዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ቀልብ የሳቡና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያሳታፉ እነደነበር ታሪክ በሚገባ መዝግቦታል።

የያኔው ወጣት ትውልድ በወቅቱ በአገራችን ውስጥ ይታይ የነበረውን ፍፁማዊ የዘውድ አገዛዝና በዓለም ደረጃም ይታይ የነበረውን የቅኝ ግዛትን ክስተት ይቃወም ነበር። በሀገራችንም ይታይ የነበረውንም ጭቆናና የመብት ረገጣ እንዲሁ አጥብቆ ተቃዉሟል ። ድኻው ይማር፤ ድኽነት ወንጀል አይደለም፤ መሬት ለአራሹ፤ ሁሉም ዜጋ በእኩልነት ይታይ፤ የሀገር ሉዓላዊነት ይከበር ፤ ሕክምና፣ ሥራ ወዘተ... ለሁሉም ዜጋ ይዳረስ፤ የብዙኀኑ መብትና ጥቅም በዕኩልነት ይከበር፤ የመደብና የብሔር ጭቆናን ለማስወገድ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት ይፈጠር፤ የሃይማኖት እኩልነት ይኑር መንግሥትና ሃይማኖት ይለዩ ብሎ ጠይቋል። ማኅበራዊ ፍትህን ለማስገኘትና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ትልቅ ዓላማ አንግቦና ብሩህ ተስፋን ይዞ ተሰባስቧል፤ ተደራጅቷል፤ ለትግል ተሰልፏል። አፓርታይድ ይውደም፤ የኢያን ስሚዝ ዘረኛ አገዛዝ ይወገድ፤ ነፃነት ለጭቁኖች፣ ... ወዘተ ብሎ ታግሏል። ይህ ተራማጅና አይበገሬ ክፍል ነው እነዚህን ክቡር ዓላማዎች ለማራመድ በፖለቲካ ድርጅት መልክ ተደራጅቶ የዛሬ አርባ ሶስት(43)ዓመት ኢሕአፓ የሚለውን ስያሜ ያገኘውን ኅብረብሔራዊ ድርጅት በሚያዚያ 1964 ዓ.ም የመሠረተው።

በኢሕአፓ ውስጥ የተሰባሰቡት የኢሕአፓ መሥራች አባላትና በሂደት ቀስ በቀስ የተቀላቀሉት አባላት፣ ደጋፊዎች፣ የወገንና የሀገር ፍቅር ያደረባችው ቆራጥ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ያኔ ገና በለጋነታቸው የመደራጀት አስፈላጊነትን ተረድተው ኢሕአፓን ሲመሠርቱና ትግላቸውን በፖለቲካ ድርጅት ወደሚመራበት ደረጃ ሲያሳድጉ ያለምንም ጥርጥር የወገናችውን ጉስቁልናና የብዙሀኑን ብሶትና መረገጥ አይተውና ሥርዓቱ ያደርሰው የነበረው በደል አስመርሯቸውና አስቆጥቷቸው ነበር። የሕዝቡን ጥያቄዎች አንግበው ዘላቂ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ ከመጣር ውጭ ሌላ ዓላማ አልነበራቸውም። ትግላቸው ብዙ ደንቃራን ብዙ ችግርን አዝሎ የነበረ ቢሆንም ወደኋላ አልጎተታቸውም።

ኢሕአፓ በተመሠረተበት ወቅት በኢትዮጵያ ስለ አደረጃጀትም ሆነ ስለ ፖለቲካ ትግል በአርዓያነት ሊያገለግለው የሚችልና ተመክሮውንም በማገናዘቢያነት ሊጠቀመበት የሚችል ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም። በመሆኑም የኢሕአፓ ምሥረታ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍቷል። የተበደለውን ሕዝብ ብሶት ብሶቴ ብሎ ፤ በተደራጀ መልክ የሕዝቡን ችግሮች ለመፍታትና ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የመላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የወደፊት ሕይወት ለማሻሻልና ሀገሪቱ ካላቸበት ኋላ ቀርነት ለማላቀቅ

ቆርጦ መነሳቱና በቅንነት መታገሉ በማንም ሊታበልና ሊካድ የማይችል ሐቅ ነው። ያ በኢሕአፓ ውስጥ ተሰባስቦ የነበረው ትውልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀሳቡን የመግለፅና የመደራጀት መብት እንዲያገኝ፤ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ ተጭነው የነበሩት የመደብ፣ የብሔረሰብ፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ .... ወዘተ ጭቆናዎች እንዲወገዱ በቅንነት ፈልጎና አስቦ፤ አስፈላጊ መሠረታዊ ለውጦችን ለማምጣትም አልሞ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል በርግጠኝነት የተነሳ ትውልድ ነበር። ከምስረታው በኋላ ኢሕአፓ ማንነቱን ያሳየው እታገልለታላሁ፤ መከራን እቀበልበታለሁ ፤ እሰዋለታለሁ ብሎ የተነሳለትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ፣ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን በማደስ፣ ማንነቱን ገላጭ የሆነውን ወኔውንና ፅናቱን ተላብሶ ትግሉን በመቀጠል ነው። ለኢሕአፓ ጽናትና ኢትዮጵያዊነት ምስክር መጥራት ካስፈለገ፣ ምስክሩ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ።

ኢሕአፓ በረዥሙና በመራራው የትግል ሂደት ለሕልውናው ማጠየቂያ የሆነውን የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ተንከባክቦ ያቆየ ሲሆን ፤ በጀግንነትና በመስዋዕትነት የጻፈውንም የአርባ ሦስት ዓመት የትግል ታሪክ በእውቀት ለማዳበር ችሏል። የፍትህን፣ የዲሞክራሲን፣ የእኩልነትንና የሀገር ሉዓላዊነትን ብርሃን በሀገሪቱ ለማብራት ሲታገልም ሁሉንም የኢትዮጵያ ልጆች በማሰባሰብ ባንድ ሀገራዊ ሰንደቅ ሥር በማሰለፍ ጭምር ነው። የኢትዮጵያ እናቶች ክብርና ምሥጋና ይግባቸውና በኢሕአፓ ምሥረታ ወቅት በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ የነበረውን በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ አኩሪና አንጋፋ የበኩር ልጅ የሆነውን ኢሕአፓን ፀንሶ የመሠረተውን ጀግና ትውልድ አበርክተውልናል።

ኢሕአፓ ስሙ እንደሚጠቁመው የሕዝብ ፓርቲ ነው። በድርጀቱ ጥላ ሥር ተሰባስበው የታገሉት አባላቱ ብሔረሰብ፣ፆታ፣ ሃይማኖት ሳይለያቸው፤ ከጠባብነትና ከትምክህት ተቃርነው፤ በሕዝብ እኩልነት አምነው፤ ኢትዮጵያችን የሁሉም የደስታ ቤት እንድትሆን ይመኙ የነብሩ ዜጎች እንጂ ዛሬ አንዳንድ የታሪክ ቀልባሾች ለመናገር እንደሚከጅላቸው ኢትዮጵያን ለመጉዳት የተሰለፉ አልነበሩም። የኢሕአፓ የትላንቱም ሆነ የዛሬ መለያው ለብዙኃኑ ሕዝብ ጥቅምና ለሀገር ሉዓላዊነት መቆሙ እንደመሆኑ መጠን፤ ትናንትም ሆነ ዛሬ ሕዝቡን ለመጨቆንና ለመከፋፈል ሀገሪቱንም ለማዋረድና ለመበታተን የፈለጉ ክፍሎች ፓርቲውን ለማጥፋት ሲማስኑ ከርመዋል። ኢሕአፓ ለገንጣዮችና ለጸረ ኢትዮጵያ ባዕዳን ኃይላት ቢያመች ኖሮማ ለዓመታት ለማውደም ጥረት ባላደረጉ ነበር።

በትግል ወላፈን ተፈትኖ ያደገና የኖረ ትውልድ ያሳለፋቸውን አርባ ሦስት (43) ድፍን የትግል ዓመታት መለስ ብለን ስንቃኝ፤ ፋሽስታዊው የደርግ አገዛዝና ጋሻ-ጃግሬዎቹ ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው በለውጥ ፈላጊው ኢትዮጵያዊ በተለይም በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ይህ ነው የማይባል ጭፍጨፋና ግድያ፤ እስራትና ሰቆቃ ፈፅመዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ አባላቱ አካለ ጎደሎ የሆኑበት፤

ክቡር ለጋ ህይወታቸውን ያጡበት፤ ብሩህና አዲስ ተስፋን ለሀገሩና ለሕዝቡ አንገቦ የተነሳ ትውልድ የተመተረበት የጥፋትና የጨለማ ዘመን ነበር። ምንም እንኳን የአገዛዙ ፍላጎት ኢሕአፓን ለመደምሰስ ቢሆንም እነሱ እንዳሰቡት ኢሕአፓ የሚጠፋ አልሆነም። ዓላማውም ሆነ ተግባሩ ሕዝባዊ ስለሆነ በየተራ የተሰሰዘነረበትን የፋሽስቶች በትር ሁሉ ተቋቁሞ ያነገበውን የትግል ዓርማ ከፍ አድርጎ ከባድ መሥዋዕትነትን እየከፈለ ያለመታከት ትግሉን በፅናት ዛሬም ቀጥሏል።

ዛሬም ኢሕአፓን የማጥፋትና ታሪኩን የመበረዝ ዘመቻ በሰፊው እየተካሄደ ነው። ወያኔ ገና ሲጠነሰስ ጀምሮ በጠላትነት የፈረጀውንና " የታላቂቷ/ አባይ/ ኢትዮጵያ " አራማጅ ነው ብሎ ይከሰው የነበረውን ኢሕአፓን ለማጥፋት ያልቧጠጠው ጋራ፤ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም። ወያኔ በአሲምባ በኢሕአፓ ላይ ሲዘምት ሻዕቢያን የዘመቻው ደጋፊና አቀነባባሪ ማድረጉ  የሚያስገርም አልነበረም። እነዚያ ጣምራ ጠላቶች ኢሕአፓን በእንጭጩ ለመቅጨት መጣራቸው የሚያመለከተው ነገር ቢኖር የድርጅቱ የጸና ሕዝባዊና አገራዊ አቅዋም  ማለትም ኢሕአፓ በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነትን መምረጡ ለመገንጠል ዓላማቸው እንቅፋት ይሆናል የሚል ከፍተኛ ስጋት እንደነበራቸው ነው። ይህንኑ ሐቅ ዛሬ የወያኔ አመራር የነበረው ግለሰብና እንዲሁም  የሻዕቢያው ዋና አለቃ መስክረውታል። በዚሁ በቀጣይነት በተደረገው  ኢሕአፓን የማጥፋት ዘመቻ ወያኔ በጎንደርና በጎጃም በኢሕአፓ ላይ ሰፊ የጦርነት ዘመቻን አካሂዶ በርካታ የኢሕአፓ አባላትን የገደለ ሲሆን በውጊያ የማረካቸውን የድርጅቱን የከፍተኛ የአመራር አባላት ያለአንዳች ፍርድ በጭካኔ መረሸኑን ምስጢር አዋቂው የቀድሞ የወያኔ መሪ በቅርቡ  በጻፈው መጽሐፍ ይፋ አድርጎታል።

ከላይ በተጭባጭ ለማስፈር እንደተሞከረው ወያኔ በዚሁ ድርጊቱ የኢሕአፓም የኢትዮጵያም ጠላት መሆኑን በግልጥ አስመስክሯል። ባሁኑ ወቅት ወያኔ እንደመጀመሪያው ጠላት (ደርግ) የፍየል ወጠጤን ከበሮ እየጎሰመ፤ በየአደባባዩ እየፎከረና እየለፈለፈ ባይሆንም ድምጹን አጥፍቶ በርካታ የኢሕአፓን አባላትና ደጋፊዎች፣ እንዲሁም ሀገር ወዳድ ታጋዮች እየገደለና እያሰረ፣ ደብዛቸውንም እያጠፋና እያሰቃየ ይገኛል። ዛሬም ይህ ሁሉ ያላባራ ግፍና በደል እየተፈፅሙበት፤ ኢሕአፓ የወያኔን እመቃና አፈና ተቀቁሞ፤ ቀጣይና ልዩ መለያው የሆነውን ብሩህ ራዕዩን ሕልው ለማድረግ ከሕዝብ ጋር ሆኖ በፅናት መታገሉን ቀጥሏል። ዛሬ ኢሕአፓ የተመሠረተበትን አርባ ሦስተኛ(43ኛ) ዓመት ሲዘክር "ትግላችን ይቀጥላል!" የሚለው ከተግባር፣ ከትግልና ከመስዋዕትነት ርቆና ተጨባጭ ትግልን በምላስ ጦርነት ተክቶ ሳይሆን ፤ ዛሬም እንደትናትናው ከሕዝብ መሀልና ጎን በመገኘት የገፈቱ ቀማሽ በመሆን እየታሠረ፣ እየተወገረና ደሙን እያፈሰሰ ነው።

ኢሕአፓ በረዥሙ የትግል ሂደቱ አንዴም ቢሆን ሕዝብን ከዶ፣ በጥቅም ተገዝቶ፣ ከጨቋኞች ጋር አብሮ፣ በሕዝብ ላይ በደል አልፈጸመም። ዛሬ ለከፋፋዩ ቡድን እያረጠረጡ የሥልጣን ፍርፋሪ ተቀራማቾች የሆኑት ትላንት ለባዕዳን አድረው የሀገርን ክብር የሸጡ አልነበሩምን? ዛሬ የትግል አባወራ ነን ብለው እየቧረቁ ሕዝቡን (የአንድነት ኃይሉን) እየከፋፈሉ አሳፋሪና በዘቀጠ መስመር እየነጎዱ፤ ኢሕአፓን ለማውግዝ የሚቃጡትስ ቢሆን ትላንት ውሏቸው የትና ከማን ጋር ነበረ? የፈሪ ጡሩምባ ሳይነፋ ያስመሳዮች ጥሪ ነጋሪት ሳይጎሽም ከትግሉ ጎራ የራቁ አልነበሩምን? ይነቀፍም ይመስገንም ኢሕአፓ፤ በትግሉ መስከ ተገኝቶ ቆስሎ፣ ደምቶ፤ ተሰቃይቶ፣ ሞቶ፣ ለሀገር ለወገን ሲል መከራን ተቀብሎ፤ ተሰውቶ፣ በደሙ የጻፈው፤ የማይሻር፣ የማይበረዝ፣ ታሪክ አለው። የሚዘከር የሚከበር ታሪክ።

የኢሕአፓ አኩሪ የትግል ታሪክ ሊመዘገብ የቻለው ለዓላማቸው ህይወታቸውን የሰጡ ቆራጦች፤ ሕዝብ ማስተባበርን እንደተልኮ የወሰዱ አደራጆች፤ ከጠባብነትም ሆነ ከትምክህት የራቁ አባላት ስለነበሩት ነው። ክቡር የሆነችው አገራችን በባዕድ ኃይል ከምትዋረድ ሞት ይሻለናል የሚሉ አርበኞች አባላት ስለነበሩት ጭምር ነው። ዛሬም አስከፊው የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ የሚቻለው በተባበረ ሕዝባዊ አመጽ ብቻ ነው በሚል ትግላችውን ቀጥለዋል። የኢሕአፓ የምስረታ ዓመት ዝክር፣ የሕዝብን ገንዘብ በሚሊዮን የሚያጠፋ ሳይሆን የመስዋዕት ታሪክን በቀጣይ ትግል ቃልኪዳን የሚያድብ የሕዝብ የራሱ ትዝታ ነው። ዛሬም ባነጋገር "የኢሕአፓ ጊዜ" መባሉ፣ የጽናትና ቆራጥነት መከሰቻ የሆነው ኢሕአፓ አሁንም ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ቆሞላታል ለማለትም ነው። ይህ ሁሉ ግን የራስ ሙገሳ ጥረት አይደለም -- ሐቅን አስፍሮ የመቀጠል እንጂ፡፡ ውድ ህይወትን የገበረ ትውልድ ደግሞ ቢወደስ ቢደነቅ ጉራ ሳይሆን ተገቢ ዝክር ነው። በዚህ ቆራጥ ድርጅት ሥር ተሰልፈው ለሕዝብ፣ ለሀገር የታጋሉ፤ የተሰቃዩና የተሰዉ ሁሉ ክብርና ሞገስ የሚገባቸው ናቸው።

ኢሕአፓ ገና ከጠዋቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲና እኩልነት እውን መሆን የታገለና እየታገለም ያለ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን፤ አንድነት ሲልም በዚሁ ላይ ተመሥርቶ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ ጠባቦችና ትምክህተኞች የሚያወግዙትም በዚሁ የተነሳ ነው። ኢሕአፓ ሲመሠረት ይዞት የተነሳውና ሲታወጅ ለሕዝብ ያስተላላፈውም መልዕክት “ ኢሕአፓ ከሕዝብ ጎን የቆመ ጠበቃ እንጂ ሕዝብን የሚተካ ነገረ ፈጅ አይደለም። ከፊት የተሰለፈ መንገድ መሪ፣ የጠላትን ቅስም ሰባሪ እንጂ በሕዝብ ስም የሚመጻደቅ ፎካሪ አምባገነን ኃይል አይደለም” የሚል ነበር። ኢሕአፓ ይህንን አቅዋሙን ዛሬም አልቀየረም። ኢሕአፓ ለሕዝብ የሚታገል የሕዝብ የትግል መሳሪያ ታማኝና ታጋይ ድርጅት ነው። በትግል ውጣ ውረድ ማለፍ ትርጉሙና ጠቀሜታው ተመክሮን ገምግሞ ስህተትን አርሞ ቃል ኪዳንን

አድሶ የተጀመረውን ከመቀጠል ጋር የተያያዘ ነው። ሕዝብን በጎጥና በሃይማኖት፣ ... ወዘተ የሚከፋፍል ወሮበላ ቡድን ሥልጣን ላይ ባለበት ሁኔታ የሕዝብ ወገን ነኝ እያለ ሕዝብን የሚከፋፍል አይፈልግም። ሀገር ልትጠፋ ነው በተባለበትና በሥልጣን የተሰየመውም ቡደን ይሁነኝ ብሎ ሊበትናት በሚቅበዘበዝበት ወቅትም የሐቀኛ ዜጋ ግዳጅ፣ በመራራው ትግል በተግባር በመሰማራት ተፈላጊውን መሰዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀት፤ የፖለቲካ ብስለትን መላበስ ፤ በስልት የመታገል ጥበብን መማር፤ ለምን? ማንንና? እንዴት መታገል እንደሚገባ ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል።

ኢሕአፓ ግዳጅ የሆነውን ሀገራዊ ትግል ለመቀጠል መጽሐፍ ገላጭ ሰላልጠበቀ፤ ትግል ባለበት ዛሬም በሰማዕቱ ክቡር ደም የቀላው ሰንደቁን--የወያኔ የክህደት ባንዲራን ሳይሆን-- ያውለበለባል። የዛሬ አርባ ሶስት ዓመት የተነሱ የሕዝብ ጥያቄዎችና መሠረታዊ መብቶች ገና ስላልተረጋገጡ፤ ይባስ ብሎ የሀገር ህልውና ራሱ ለአደጋ በመጋለጡ ቃል ኪዳንን አድሶ ጸረ-ወያኔ ትግልን መቀጠል ለዚህም ሕዝብን ማሰባሰብና አደራጅቶ ማታገል ለመጭው ትውልድ አይለጉት ግዳጅ ሆኖ ይገኛል። ኢሕአፓ ይህንን ግዳጅ ያኔ ገና ሲመሠረት እንደተቀበለው ሁሉ ዛሬም ዋና ግዳጁ ነው፤ ወደ ሌላ አይለጉት ሀኬት ነው ብሎ ተቀብሎ በትግሉ በጽናት ቀጥሏል። ይህ የዛሬው ትውልድ ግዳጁን ካልተቀበለ ግን፤ በሰበብ አስባቡ ከተልፈሰፈሰ ግን፤ ለወያኔ በቀጥታም በስውርም ከተገነበሰ ግን ሀገራችን ለከፋ አደጋ መዳረጓ አይቀሬ ይሆናል። ኢሕአፓ የትግል ፋኖስ መቸም እንዳይጠፋ ሲታገል የቆየና አሁንም የሚታገል ነውና ለ43 ዓመት ትግል ሲል ጊዜ ቆጠራ ሳይሆን በደም በመከራ የታለፈንና የተጻፈን ታሪክ የሚያስታውሰውና የሚዘክረው ለአዲሱም ትውልድ ትምህርት ይሁን በሚል ነው። በተለይም ዛሬ ጸረ-ኢሕአፓ ዘመቻ በወያኔ አነሳሽነት በስፋት እየተካሄደ ነውና።

አሁን መለስ ብለን ኢሕአፓ የነበረውን ቦታና ሚና፤ ሚዛንና ጠቀሜታ ስንዘረዝር በነበር ለመኩራራት ሳይሆን የነበረውን ለማስታወስና የሀሰትን ጉም ገልጦ ሐቁን ለማሳየት ነው። የመጀመሪያው ይፋ የሆነ ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ ስንል ሐቅ ነው። የራሱን ራዲዮ--ፍኖተ ዴሞክራሲ-- ነጻ ባወጣው ግዛት አቋቁሞ ሕዝብን የቀሰቀሰና አሁንም የፍኖተን ህልውና አስቀጥሎ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። የሴቶችን የመደራጀት ጥረት ማገዝ ፤ ሰርቶ አደሩን ላባደሩን ለወሳኙ ትግል ማዘጋጀት፤ ጭቁን ወታደሮችን ማደራጀት፤ ከድርጅት አልፎም ወሳኝ በሆነውና መስዋዕትነትን በሚጠይቀው ትግል መሰማራትና አኩሪ ታሪክ መስራት--ይህ ሁሉ ኢሕአፓን ገላጭ ሆኖ የቆየ ነው። ያለፈውን ታሪክ ስንዘክር፣ ስንገመግም ደግሞ መነገር ያለበትን የተፈጸመውን ገድል ብቻ ሳይሆን ስህተትንም --ትምህርት ነውና-- መጥቀስ አስፈላጊ ነው። በትግል የተሰማሩ ደግሞ ስህተት መፈጸማቸው አይቀርም-- ትግል ተጋድሞ ልፈፋ አይደለምና። በመሆኑም ድርጅቱ መንሰኤው ለኢትዮጵያ ስርየት ነበርና ይህን ክቡር ዓላማ ይዞ

ሲታገል ከተመክሮ ማነስ ስህተት መፈጸሙ የሚጠበቅ ነው። ይህን በሚመለከትም የፈጸማቸውን ስህተቶች የዛሬ 35 ዓመት ገምግሞ ለሕዝብ ያቀረበ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ባንጻሩ አረመኔ ደርግን መታገል ስህተት ነበር፤ መስዋዕት መክፈል የማይገባ ነበር፤ ለደርግና ለባዕድ መንበርከክ ጥሩ ዘዴ ነበር የሚሉትን ተቀብሎ ስህተት ፈጽሚያለሁ የሚል አይደለም። ይህን የሚጠብቁ ካሉ ጦማቸውን ያድራሉ። በተመክሮ ማነስ ግን ሀገር ሊታደግ ሲጥርና አረመኔዎችን ሊያወድም ሲሞክር የፈጸማችውን ስህተቶች ከሁሉም ቀድሞ ያመነና ግለ ሂስ ያደረገ ድርጅት ነው። እስካሁንም ድርጅቱ ራሱን መመርመርና የብዙሃንንም ውሳኔ መሰረት አድርጎ በቀናው ጎዳና መጓዝን የሚያምንበት ቢሆንም በየጊዜው፤ በረጅሙ ውጣ ውረድ አያሌ እንቅፋቶች አደናቅፈውታል። መርሁን የሚጻረሩ በግል ፍላጎት ብቅ ብቅ እያሉ ሊያዳክሙትም ጥረዋል። ይህና የለየላቸው ጠላቶች ጥቃትም ጉዳት ሲያደርሱበት መቆየቱም የሚታወቅ ነው። ሲደናቀፍ፤ ሲወድቅ ግን ድርጅቱ ሁሌም በአባላቱ ጽናትና በሕዝብ ድጋፍ ሰንደቁን ከአፈር ሳይደባልቅ ከወደቀበት እየተነሳ ትግሉን ቀጥሏል። ይህንን ነው አርባ ሶስት ዓመት ሲል ክብደት ሰጥቶ የሚያቀርበው።

ኢዳዲስና ያልተለመዱ አደረጃጀቶችን አምጥቶ ሰፊውን ሕዝብ በትግሉ አሳታፊ እርምጃዎችን ወስዷል። ሴቶች መብታቸውን እንዲያስከብሩ በራሳቸው በጾታ ደረጃ እንዲደራጁ ያደረገው ጥረት ቀላል አልነበረም --በርካታ ሴቶችም በዙሪያው ተሰልፈው ታግለው ተሰውተዋልም። ኢትዮጵያን በማስቀደም ዴሞክራሲና እኩልነትን መሠረት በማድረግ የኅብረ ብሔራዊ ድርጅትን መንገድና አማራጭነትን አሳይቶ ገና ከጠዋቱ ጠባቦችን ሆነ ትምክህተኞችን ታግሏል። አፄው መለኮታዊ ሥልጣን አላቸው በሚባልበት ሀገር፣ የፍጹም ስልጣን ባለቤት ጭቁኑ አፈር ገፊውና በላቡ አዳሪው ሕዝብ ነው ብሎ ደፍሮ ተጋፍጧል። የአጼውን ሥርዓትም ሆነ ጨቋኝ ገዢዎችን በሕዝባዊ ትግል ማስወገድ ይቻላል ብሎ ያኔ፣ ገና ያኔ የተነሳና እምቢኝ ያለ ኃይል ነው። በመሆኑም ሞተ ሲሉ እያሳፈራቸው፤ ተበተነ ሲሉ እየተሰባሰበባቸው ፤ ትግሉን በመቀጠሉ ኢሕአፓ የሕዝብ አለኝታ ሆኖ ባጅቷል። ድምጹንም ለሕዝብ ሲያሰማ ዓመታትን አስቆጥሯል ። በትግሉ ላይ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች በጽናት መቀጠሉን ያረጋግጣሉ። ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልጽ እንደሆነው፣ ወያኔ 40 ዓመት ሆነኝ በማለት የሕዝብን ገንዘብ አፍስሶ የትግራይ ድል የሚለውን የሚያከብረው ከደደቢት እስከዛሬ የሕዝብን መብትና ነጻነት በማፈን ፤ በጸረ-ኢትዮጵያነት የቆየባቸውን የክህደትና የወንጀል ዓመታት ለማስታወስ ነው። ኢሕአፓ ግን 43 ዓመት ሞላኝ ሲል ይህን ሁሉ ዓመታት በትግል ማሳለፍ ከባድ ሆኖ ቢታይም በሚያኮራ ሀገር አድን በሆነና የሕዝብን መብትና የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ ዓላማ ባደረገ ቆራጥ ትግል ላይ ተሰማርቶ መቆየቱን ለማስታወስ ነው።

መድብለ ፓርቲን ከነቃሉ ያስተዋወቀው ኢሕአፓ በጊዜው ብቸኛ ፓርቲ፤ ግንባር ቀደም ፓርቲ ይባል የነበረውን ቀይሮ በጋራ ለመታገልና መድረኩንም ሰፊና ሁሉን አቀፍ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። በዚህም መሠረት የብዙ የኅብረት ጥረቶች መሃልና አካል ሆኖ የታገለና የተንቀሳቀሰ መሆኑንም ታሪክ መዝግቦለታል። በአሁኑ ጊዜ እርባና ቢስ በሆኑ የስብስብ ጥረቶች አልካፈልም ብሎ ገለል ቢልም በሀገር አንድነት ከሚያምኑና የሚታይ ህልውና ካላቸው ጋር በተቻለውና ሁኔታው በፈቀደው ለማበርና ባጠቃላይና በተለይም በሀገር ውስጥ ተባብሮ ለመሥራት ፍላጎቱን በተደጋጋሚ ገልጧል። በዚያው መንገድ ደግሞ ሁነኛ የሆነውን ሰፊውን ሕዝብ አቅፍ አሰባሳቢ አቅዋም ይዞ አረመኔውን የወያኔ አገዛዝን ለመታገል በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለመጪው ትውልድ አይለጉት ሀኬት እንደተባለው ነው። ላለፉት 24 ዓመታት በኢትዮጵያ ዋና መገለጫ ቅራኔ ሆኖ የቆየው--ማለትም የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ከጨቋኙ ወያኔ ጋር አቃርኖ ያለው ሁኔታ-- አልተለወጠም። ወያኔ በአያሌው ቢዳክርም የሕዝብ የእርስ በርስ ልዩነት ሆነ ቅርኔ መለስተኛ እንጂ ዋና አይደለም። ስለዚህም የትግላችን ዋና ትኩረት የወያኔን አገዛዝ ማረቅ፤ ወኔሻ መውሰድ ሳይሆን ማስወገድና እንዲከትም ማድረግ ሆኖ ይገኛል ።

ትግሉ የሚንቀሳቀሰው፣ ሕዝብን ተጻሮ ከቆመ ኃይል ጋር መሞዳሞድን በመምረጥ ሳይሆን በጥላቻ-- አዎ በጥላቻ--አምርሮ በመታገል ብቻ ነው። በየካቲት 66 ጊዜ ኢሕአፓ ባወጣው መርሃ ግብር፣ ዴሞክራሲያዊ መብት ከተጠበቀ በሰላማዊ መንገድ የሚታገል መሆኑን ቢገልጽም ይህ ለገዢዎቹ ስላልጣመና ወደ አፈናና ሽብር መጓዝን በመምረጣቸው ለብረት ትግል ኢሕአሠን መመሥረትና በከተሞችም ቢሆን በዋና መልኩ የመከላከል እርምጃን ለመውሰድ ተገዶ ነበር ። የትግል ስልትን የሚወስነው ተጨባጩ ሁኔታ እንጂ፤ የገዢው ክፍል ፖለቲካ ወይም ሌላ አይደለም። ጭፍን አምባገነንነት በሰፈነበት ሰላም፣ ሰላማዊ ትግል ብሎ መፈጠም ብልህነት ሳይሆን ራስን ሰለባ አድርጎ ማቅረብ ትግልንም መጉዳት ነው። ማመጽ የሕዝብ የማይገረሰስ መብት ነው። የፖለቲካ ሥልጣንና መብት ከወያኔ ምርጫ ሳጥን ይገኛል የሚሉት፤ የ1997 ቱን ሁኔታ የረሱ ናቸው ቢባል ስህተት አይሆንም። በመረጡት መንገድ የመከነፍ መብታቸውን ሳንጋፋ፤ በአንጻሩ ግን ሁለገብ ትግልን የሚነቅፍና የሚያጥላላ ሀሳብን የምንቀበል አይደለንም ፤ አልነበርንም። በ43 ዓመታት ትግላችን ያየነው ገዢዎች ልመናና ምለላ፤ ምርጫና ጭምትነት ልባቸውን የሚያራራ ሳይሆን ባልጩት የሚያደርግ መሆኑን ነው። ወያኔ በተለይ የሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድን ዘግቶ፤ የንጹሃን ደም አፍሶ የተሰየመ ሕገ ወጥ አገዛዝ ነውና ከእባብ ዕንቁላል ርግብ ይወለድ ዘንድ መጠበቁ ያስመርዛል፤ ይጎዳል በሚል ኢሕአፓ በጽናት ታግሏል። በየጊዜው ለማባበል ለሞከሩትም አልተበገረም። ደርግንም ወያኔንም ጠንቅቆ የሚያውቀው ኢሕአፓ ሲደልሉት ሆነ ውዥንብርን ለማስፈን ሲጥሩ እሺ አላላቸውም። ለ43

ዓመት የቀጠለው ሕዝባዊና የጸና አቅዋሙም ይህ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን ተቀዳጅቶ የኔ የሚለውን መንግሥታዊ አስተዳደር በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሲሰይም ይህን አቅዋሙን ይቀይራል - ግን ይህ ዕውን ሲሆን ብቻ !

ዝንጀሮ ከበዛ ይወረዛል ገደል፣ ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል ነውና፤ ያልተገላበጠም ያራል ነውና ኢሕአፓ ዕድሜውን ሁሉ በዓመጽ አሳልፏል። የሕዝብን ጠላቶች ሁሉ ባለው አቅም ታግሏል። እግሩ ለጠጠር ግንባሩ ለጦር ሆኖ ከርሟል። የልጅ ሰነፍ ሆኖ ሀገሩን አላሳፈረም። ጀምሮ የማይፈጽም አይደለምና ዛሬም ለሕዝብ የገባውን ክቡር ቃል ኪዳን አክብሮ ትግሉን ቀጥሏል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!